# የሙሉቀን መለሰ እጅግ አሳዛኝ ሕይዎትና
# የጥላሁን ገሰሰ የብቃት ማነስ!

በ16 እና ትናንትና በ23,11,2009 ዓ.ም. ኢቢኤስ በተባለው ቴሌቪዥን (ምርዓየኩነት) የእንጨዋወት ትዕይንተ ወግ (ቶክ ሾው) ዝግጅት ላይ የቀድሞው ከያኔ ጋሽ ሙሉቀን መለሰ ከከያኔ ዓለም ፀሐይ ወዳጆ ጋር እንግዳ ሆነው ቀርበው ነበር፡፡ ጋሽ ሙሉቀን ሕይዎቱ እንዲህ በሕመምና በችግር የተሞላ አይመስለኝም ነበረ እጅግ በጣም ነው ያሳዘነኝ፡፡ ከዚህም ባሻገር ይህ ቃለምልልስ ለጋሽ ሙሉቀን የነበረኝን ግምት በእጅጉ ጎድቶ ለሱ የወረደ ግምት እንዲኖረኝ ነው ያደረገኝ፡፡ እንደኔ ሁሉ ሌሎቻቹህንም እንዲህ እንዳደረጋቹህ ይሰማኛል፡፡ እኔ ጋሽ ሙሉቀን ይመስለኝ የነበረው ልክ ይሁንም አይሁን መርጦ የሚናገርና የበሰለ ሰው ነበር ይመስለኝ የነበረው፡፡

ጋሽ ሙሉቀን መላወስ እንኳ በሚያዳግት ደረጃ እጅግ በጣም ወፍሯል! ያው ውፍረት ሲመጣ ተከትለው የሚመጡ የጤና ችግሮች ስኳር፣ ደም ግፊት... አምጥቶበት ለተወሳሰበ የጤና ችግር በመዳረጉ በተለያየ ወቅት ከሦስት ጊዜያት በላይ ቀዶ ጥገና ተደርጎለት እንደነበር ተናግሯል፡፡ ጋሽ ሙሉቀን ጾም የሌለበትን ዘመን አመጣሽ እምነት መሰል ተቋም መቀላቀሉና እንዳገኘ መጥረጉ ለእንዲህ ዓይነት ውፍረት እንደዳረገው በግልጥ ማየት ይቻላል፡፡ ለነገሩ አሁን አሁን የፕሮቴስታንቱ ዓለም የውጩ ሳይሆን የሀገር ቤቱ የሚቀርብባቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ ማስተባበል ባለመቻላቸው ሊጾሙ ባይችሉም እንኳ የጾምን ክርስቲያናዊ ግዴታነት ለመቀበል ተገደዋል፡፡ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከዓመቱ ሰባቱ ወራት ጾም ነው፡፡ ይሄንን በመጥላትና እንዳገኙ ለመጥረግ ሲሉ ብቻ አንዲቷንና ብቸኛዋን ሃይማኖት ይሁ. 1፥3, ኤፌ. 4፥5, ኤር. 6፥16 እየጣሉ በየቀኑ እየተፈለፈሉ አዳራሽ ተከራይተው የምንትስ ቸርች እያሉ የሚፈጠሩትን አዳዲስ ሐሰተኛ እምነት መሰል ድርጅቶችን የተቀላቀሉ ግለሰቦች በርካቶች ናቸው፡፡ ቀኑ ጾም ነው ምን ሳይሉ ባሻቸው ሰዓት ያሰኛቸውን ምግብ የጾም የፍስክ ሳይሉ እንደልባቸው ከመጥረግ ልክ እንደ ጋሽ ሙሉቀን ከልክ ያለፈ ውፍረትንና ተከትለው የሚመጡትን በሽታዎች እንጅ ምን የሚያገኙ መስሏቸው ይሆን?

ጋሽ ሙሉቀን በዚህ ቃለምልልሱ በሱ ጉዳይና ተናገራቸው በሚባሉ ነገሮች ላይ ይነሡ የነበሩ ጉዳዮችን አንሥቶ ማስተባበያ ሰጥቷል፡፡ አሁን ባለበት ድርጅትም በሞያው ለማገልገል ዕድል ባለማግኘቱ ብሶት እንዳለበትም አንሥቷል፡፡ ለመተዳደሪያ የሚሆነው ገቢም እንደሌለውና የሰው እጅ ዓይቶ እንደሚኖር ገልጧል፡፡ በቃለ ምልልሱ ላይ በተነሡት ጉዳዮች ላይ አንዳንድ ነገር እንላለን፡፡

ጋሽ ሙሉቀን የወረደ የብስለት ደረጃውን ከገለጠበት ንግግሩ ውስጥ "እግዚአብሔር ሆይ! እንደአባቴ ቄስ እንድሆን እንደምትፈልግ አውቃለሁ፡፡ እኔ አሁን ቄስ መሆን አልፈልግም! ታዋቂ ዘፋኝና ሀብታም አርገኝና ከዚያ በኋላ እመጣልሀለሁ! ቄስ እሆናለሁ! አልኩትና ሰማኝ ታዋቂ ዘፋኝም አደረገኝ!.... ሀብታም ግን ስላልሆንኩ ሎተሪ ቆርጬ ሳይደርሰኝ ስለቀረ ተናድጀ ፈጣሪ መኖሩንም ለማረጋገጥ ብየ እግዚአብሔርን ሰደብኩት፡፡ ና! ግጠመኝና ይዋጣልንም አልኩት!" ብሎ የተናገረው ይገኝበታል፡፡ አሁን ታዲያ ይሄ ሰው ነው ከሰባት ዓመቱ ጀምሮ በእግዚአብሔር እጅ ተዳሶ የተመረጠው፣ እግዚአብሔርን የሚያውቀውና በእግዚአብሔር መንፈስ የተሞላው?

ቆይ እንጅ ጋሽ ሙሉቀን እግዚአብሔርን እንዴት ብታስበው ነው

"ተረከዘ ሎሚ ጠብደል ያለ ባት፤
ኮራ ያለ ዳሌ ሙትት ያለ አንጀት፤
ከሷ ጋር አድሬ ሲነጋ ልሙት፡፡"

እያልክ ዓለምንና ዝሙትን ኃጢአትን እርኩሰትን ለ 17 ዓመታት እንድትሰብክ ያደረገህ እግዚአብሔር እንደሆነ ልታስብ የቻልከው? ስለ እግዚአብሔር ያለህ እውቀትና ግንዛቤ ይሄንን ያህል የተሳሳተና የወረደ ነው ማለት ነው?

ጋሽ ሙሉቀን ቀጠለና "በሰባት ዓመቴ" አለ ጋሽ ሙሉቀን መለሰ፡፡ በሕልሙ እንዳይመስላቹህ በእውኔ ነው የሚለው "አንድ እጅ ከሰማይ መጥታ ግራ ደረቴ ላይ ገባችና የነበረውን አንሥታ ሌላ አስቀምጣ ተመልሳ ስትሔድ አየሁ!" አለ፡፡ አቶ ሙሉቀን ይሄንን የሚለው ፌጥሮ ካልሆነ ያ ያየው እጅ የሰይጣን እጅ ለመሆኑ ከዚያ በኋላ በሱስ ማጥ ተነክሮ ያሳለፈውን፣ ዓለምንና ዝሙትን እርኩሰትን በዘፈን የመስበክና በርካቶችን በዓለም ማጥ እንዲዘፈቁ የማድረግ ተግባር ከዚያም ... የሆነበትን ሕይወት ሁሉ ልብ ብሎ ማየቱ ብቻ በቂ ማስረጃ ነው፡፡

አሁንም ቢሆን ጋሽ ሙሉቀን የተናገራቸውን ነገሮች ስናጤን ለምሳሌ "ባለፈው ጊዜ ባጋጣሚ ዘፈኔን ከሰው ቤት ሰምቸው እንባየ መጣና አለቀስኩ ማለቱን፣ "ዘፈን ኃጢአት እርኩሰት ነው እነዚያን ዘፈኖቸን በመዝፈኔ እጸጸታለሁ!" ያለ ሰው ዘፈኖቹን መሥራት የሚፈልጉ ከያኔያን ሳያስፈቅዱትና እርሜ ናቸው ካላቸው ዘፈኖች ከፍያ መጠበቁን ወይም ሳይከፍሉት እንዳይሠሯቸው ማስጠንቀቁንና ዘፈኖቸ ልጆቸ ናቸው ማለቱን ስናይ፣ ዝሙትን እርኩሰትን ስለሚሰብኩ "የጌታ ነኝ!" ብሎ የሚያወግዛቸውን ዘፈኖቹን የሚመለከተው የመንግሥት ተቋም በሙዚየም አስቀምጦ የኢትዮጵያ ሀብት አድርጎ ጥበቃና እንክብካቤ እንዲያደርግላቸው መጠየቁን ስናይ ጋሽ ሙሉቀን ዘፈንን በአፉ እንጅ ከልቡ እንዳልተወና "የጌታ ተከታይ ነኝ!" ብሎ ስለሚለው ነገርም ምንም የሚያውቀው ነገር እንደሌለ እንረዳለን፡፡ ሰውየው መንተፍረት ይዞት ዘፈንን ተውኩ ብሎ በዚያው ቀረ እንጅ ሁለነገሩ ያለው ከዘፈን ጋር ነው፡፡

ስለ ጋሽ ሙሉቀን የቀደመ ሕይወት ሳጠያይቅ ያገኘሁት መረጃ ምንድን ነው መሰላቹህ፦ ሰውየው በቅላቱና በመልኩ ይታበይ፣ ይኮራ፣ ሰውን ይንቅ እንደነበር፣ "እኔ እንደናንተ አይደለሁም ከእናንተ የተለየሁ ነኝ!" እያለ በሐበሻ ወይም በገዛ ወገኑ ላይ ይታበይ ወይም እራሱን ያመልክ እንደነበር ሰምቸ ነበር፡፡ አሁንም በዚሁ በቃለምልልሱ "... እኔ ስፓኒሽ የመሰልኩ ሰውየ... የምሞትና ሰው የሚሆነውን ሁሉ የምሆን አይመስለኝም ነበር፡፡ መጨረሻህ ምን ይሆን? እያልኩ እራሴን እጠይቅ ነበር..." በማለት እራሱ አረጋገጠልኝ፡፡ ለመናፍቅነት የዳረገውም ይህ እራሱን ከነጮች ጋር የማዛመዱ፣ ሐበሻን የመናቅ በሐበሻ ላይ የመታበይ አስተሳሰቡ እንደሆነ እገምታለሁ፡፡ ለማንነቱ ከፍ ያለዋጋ የሚሰጥ ሰው፣ በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራና ከኢትዮጵያዊነቱ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው ሰው የፈለገ ነገር ቢሆን ሃይማኖቱንና ማንነቱን አይጥልም፡፡ ሰውየው ለሐበሻ፣ ለማንነቱ ክብርና ዋጋ የማይሰጥ ይልቁንም የሚንቅ፣ እራሱን ከማንነቱ ያጨነገፈ ሰው በመሆኑም ነው እንደነ ጥላሁን ገሰሰና ሌሎቹ የዘመኑ ከያኔያን ተጠቃሽ የሆነ ስለሀገር ፍቅርና ስለ ልዕልና ስላለው ማንነታችን የዘፈነው ዘፈን ሊኖረው ያልቻለው፡፡

ጋሽ ሙሉቀን የሚታወቀው በፍቅር ስም ዓለምን በሚሰብኩ ወይም ዝሙትን፣ እርኩሰትን፣ ብልግናን በሚሰብኩ፣ ከባሕል ከወግ ከግብረገብ ባፈነገጡ ዘፈኖቹ ነው እንጅ እንደ ሌሎች ከያኔያን ስለ ሀገር ፍቅር፣ ልዕልና ስላለው ማንነታችን፣ ግብረገብነትን ስለተሞላ ባሕላችን፣ ስለ ሥነምግባርና ሌሎች የሚያንፁ ዘፈኖችን በማቀንቀኑ አይደለም፡፡ ለዚህም ነው በቃለ ምልልሱ ላይ እንዳዳመጣቹህት ሀገሩን፣ ወገን ዘመዱን እንደማይናፍቅና መመለስም እንደማይፈልግ የተናገረው፡፡

የገረመኝ ነገር ቢኖር ጋሽ ሙሉቀን "ሀገራቹህን ወገን ዘመዶቻቹህን ጥሉ አትናፍቁ!" የሚልን ቃል ከየት እንዳገኘ ነው፡፡ ሰውየው የእግዚአብሔርን ቃል የሚያነብ ቢሆን ኖሮ የኢትዮጵያን እና የሕዝቧን ያህል በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስና ክብር ያገኘ ሕዝብ እንደሌለ ተረድቶ ሀገሩንና ማንነቱን በወደደ ነበር፡፡ የእስራኤል ልጆች እንኳ ሳይቀሩ እግዚአብሔር "የእስራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ ለኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላቹህምን?" ትን. አሞ. 9፥7 በማለት የእስራኤል ልጆችን ልክ እንደኛ አድርጎ እንጅ ከእኛ አሳንሶ እንደማያያቸው ተናገረ እንጅ ከእኛ አስበልጦ እንደሚያያቸው አልተናገረም፡፡

እንዲህ እንደ ጋሽ ሙሉቀን በማንነት ቀውስ የሚናጡ ተመሳሳይ ግለሰቦችን አውቃለሁ፡፡ በአንድም በሌላም መንገድ እንደ ጋሽ ሙሉቀን በባዕዳን ማንነት ተማርከው እራሳቸውን ከባዕዳን ጋር ለማስተሳሰር ለማዛመድ የሚጥሩ ሰዎች

ሃይማኖታቸውን ለመቀየርና ማንነታቸውን ለመጣል አሳማኝ ነገር አያስፈልጋቸውም፡፡ ሃይማኖታቸውን ማንነታቸውን እንደቀላል ነገር አውጥተው ሲጥሉት ቅንጣት ታክል እንኳ አይሰማቸውም፡፡ ነገር ግን ወደዋቸው የሔዱባቸውን ነጮችን ወይም ዓረቦችን ሆነው መሆን ስለማይችሉ ከውስጣቸው እውነታው ከፍላጎታቸው ጋር በሚፈጠረው ግጭት በሕመሙ ዘወትር እንደተሰቃዩ ይኖራሉ፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ "እናንተን ነን!" ብለው የተጠጓቸው ወይም ሊሆኗቸው የሚፈልጓቸው ነጮች ወይም ዓረቦች ከዘረኝነት የተነሣ እንደምናምንቴ ሲቆጥሯቸው የሥነልቡና ችግራቸውን ይበልጥ ያወሳስብባቸዋል፡፡ ነጭ ሳይሆኑ እራሳቸውን ነጭ እንደሆኑ አድርገው ሲመለከቱ፣ ዓረብ ሳይሆኑ እራሳቸውን ዓረብ አድርገው ሲመለከቱና አካላቸው ደግሞ ይሄንን አስተሳሰባቸውን ሲቃረንባቸው እንደሚፈልጉት ሆነው አለመገኘታቸው እንደመረቀዘ ቁስል ዘወትር እንዳሳመማቸው ይኖራሉ፡፡

በዚህ ምክንያት በአብዛኛው ጊዜ ለአእምሮ መታወክ በሽታ (mental disorder) ይዳረጋሉ፡፡ ይህ በሽታ ባስ ሲል ወደ እብደት ይቀየራል፡፡ ብዙዎቹ ግን ይህ በሽታቸው ከአእምሮ ሁከትነት ሳያልፍ ነው በሞት የሚወሰዱት፡፡ ይሄም ችግር ቢሆን ግን ቀላል አይደለም፡፡ ችግሩ ነገሮችን በትክክል ከማየትና ከመመዘን ስለሚገድባቸው የበሰለና የጠራ አስተሳሰብ አመለካከት እንዳይኖራቸው፣ ማመዛዘን እንዳይችሉ ያደርጋቸዋል፡፡ ለእውነታና ለአመክንዮ አይገዙም፡፡ ብቸኛው የማሳመኛ ወይም የመከራከሪያ መንገዳቸው ድርቅና ነው፡፡ በድርቅና ማሳመን ወይም የሚመጣባቸውን ጥያቄ መመለስ ካልቻሉ ጥለው ይሔዳሉ ወይም መናገር አይፈልጉም እንጅ በመረጃ ወይም በአመክንዮ ተረጋግጦ የቀረበላቸውን እውነታ መቀበል አይፈልጉም፡፡ ጋሽ ሙሉቀን ላይ ያስተዋልኩት ይሄንን ነው፡፡ ከያኔ ዓለምፀሐይ ወዳጆን ደጋግሞ አንገቷን እስኪያስደፋት ድረስ ጋሽ ሙሉቀን የሚናገራቸው ነገሮች በእሱ ዕድሜ ካለ ሰው የማይጠበቁና ያልበሰሉ የሆኑት በዚህ ችግር ምክንያት ነው፡፡

ጋሽ ሙሉቀን በቃለምልልሱ ስለ ጋሽ ጥላሁን ገሰሰ በተናገረው ላይ ግን እስማማለሁ፡፡ እንዲያውም ጋሽ ጥላሁን ጋሽ ሙሉቀን ያልጠቀሰው ሌላም ችግሮች አሉበት፡፡ ጋሽ ሙሉቀን ያለው "ጥላሁን ቢትና ኮርድ አይጠብቅም!" ነው ያለው፡፡ ይሄ ማለት ከዘፈን መሣሪያው ጋር ተናበ ተጣጥሞ መጫወት አይችልም ማለት ነው፡፡ ይሄ ብቻ አይደለም የጋሽ ጥላሁን ችግር እኔም በግሌ ያስተዋልኩት ጋሽ ጥላሁን በሌሎች የሚበለጥባቸው ነገሮችም አሉ፡፡ አንድ ነገርን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ የድምፅ ቁልፎችን በመንካት ደረጃ ጋሽ ጥላሁንን የሚያክል ዘፋኝ የለም፡፡ ነገር ግን ጋሽ ጥላሁን የመጮህ እንጅ የሚዘፍናቸውን ዘፈኖች ስሜት አንብቦና ተረድቶ ያለማዜም ከፍተኛ የሆነ ችግር አለበት፡፡ በርካታ ዘፈኖቹን የተጫወታቸው እነኝህን ቅመሞች ሳያገናኝ ሳያዋሕድ ነው፡፡ ስሜትን ያዘ የሚያደርግ ለስላሳ ድምፅና ቅላፄ ማምጣት በሚገባው ቦታ ላይ በኃይል እያንባረቀ በመጮሁ ከዜማና ግጥም ደራሲዎቹ ጋራ የሚጋጭባቸው በርካታ ጊዜያት እንደነበሩ ግለ ታሪኩ ይናገራል፡፡ ጋሽ ጥላሁን ትንሽም ቢሆን ለመስተካከል የቻለው በእነኝህ አስጠኝዎቹና የዜማ ደራሲዎቹ ጥረት ነው እንጅ መዝፈን ማለት ለጋሽ ጥላሁን መጮህ፣ ማንባረቅ ማለት ነው፡፡ ጩኸት ላይ በማተኮሩ ይመስለኛል የሱን ያክል የድምፅ ቁልፎችን መንካት የሚችል የለም፡፡ ይሄንን ብቃቱን ሌሎቹ ሊጫወቷቸው ከማይችሏቸው ዘፈኖቹ መረዳት ይቻላል፡፡

እስከዛሬ በርካታ የጋሽ ጥላሁንን ድምፅ በማስመሰል የተጫወቱ ድምፃውያንን አድምጠናል፡፡ ማስመሰል ስል ማስመሰል ማለቴ ነው፡፡ ማንም የማንንም ድምፅ መድገም አይችልም፡፡ ድምፃችን በተፈጥሮው እንደ የጣት አሻራችን ሁሉ የተለያየና የማይደገምም በመሆኑ፡፡ ስለዚህ የጋሽ ጥላሁንን ዘፈኖች አስመስለው የተጫወቱ ስል ምን ማለቴ እንደሆነ ልብ በሉ፡፡ ከያኔያን አስመስለው ሲጫወቱ ሦስት ዕድል ይኖራቸዋል፡፡ ጥሩ አቅምና ብቃት ካላቸው ከነበረውም አሳምረው ይጫወቱታል፡፡ ከነበረው አመሳስለው አመጣጥነው መጫወት የሚችሉም አሉ፡፡ ካልሆነም ከነበረው በወረደ ደረጃ ይጫወቱታል፡፡

የጋሽ ጥላሁንን ዘፈኖች ለመጫወት ከሞከሩት ውስጥ ማናቸውም ቢሆኑ በጋሽ ጥላሁን ደረጃ የተጫወተ የለም፡፡ ለምሳሌ "የትዝታየ እናት" ከሚለው ዘፈኑ "አይ......ይ" የሚላትን የድምፅ ቁልፍ መንካት የቻለ አይደለም የተጠጋ እንኳ የለም፡፡ ይሄ የጋሽ ጥላሁንን ከፍተኛ ብቃት ያሳያል፡፡ በሌሎች ነገሮች ግን ጋሽ ጥላሁንን በጣም የሚበልጡት አሉ፡፡ ለምሳሌ የሚዘፍነውን ዘፈን ከጆሮ ብቻ ሳይሆን ከመላ አካላት ጋር አዋሕዶ በስሜት ተመስጦ በመጫዎት ከወንዶች መርዓዊ ዮሐንስን ከሴቶች ብዙነሽ በቀለን የሚያክል ዘፋኝ የለም፡፡ በድምፅ ተሰጥኦ ማሪቱ ለገሰን፣ በድምፅ ቃና ዚነት

ሙሀባውን፣ ኩልል ባለ ድምፅ ሙሉቀን መለሰን፣ ግርማ ሞገስ ባለው ድምፁና ለዘፈኑ ውበት በመስጠት ተስፋየ ገብሬን የሚያክል ዘፋኝ የለም፡፡ ጥበብን ከዘፈን ጋር አዋሕዶ በመግለጥ ችሎታ ስለሽ ደምሴን፣ ኪነትን ለተፈጠረችበት ዓላማ በመጠቀም ብቃት ቴዎድሮስ ካሳሁንን፣ አርአያነት ባለው ማለትም ሥነምግባርና ሥነሥርዓትን በተሞላ (ዲሲፕሊንድ በሆነ) የከያኔ ሕይዎቱ ታምራት ሞላን የሚያክል ከያኔ የለም ባይ ነኝ፡፡

"ጥላሁን ገሰሰ ከዘፋኞች አንደኛ ነው!" ሲባል እነኝህን የጠቀስኳቸውን ብቃቶች ሁሉ ጠቅልሎ የያዘ ነው ማለት እንዳልሆነ ልብ የምንለው ይመስለኛል፡፡ ጋሽ ጥላሁን ከላይ ከጠቀስኳቸው ብቃቶች በአንዳንዶቹ ዜሮ ወይም ባዶ ነው፡፡ ሌሎቹ ብቃቶቹ ከፍ አድርገውት ድምር ውጤቱ አንደኛ ለመባል አበቃው እንጅ ተሰጥኦዎችን በተናጠል እንይ ከተባለ ግን አንደኛው ጋሽ ጥላሁን ብቻ ሳይሆን በየብቃታቸው አንደኛ አንደኛዎቹ በርካቶች ናቸው፡፡ ይሄው ነው አመሰግናለሁ!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው
amsalugkidan@gmail.com